«የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል።»

መዝ. ፴፫፥፯

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር

ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና

ጸሐፊ

ገነት ታደሰ

# ጦርነቱ በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም የቱሪስት ፍሰት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደሩ ተገለጠ



ቆሞስ አባ ጽጌሥላሴ መዝገቡ

ካሳሁን ለምለሙ

የበሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እየተካሄደ ያለው ጦርነት በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ ገዳም የቱሪስት ፍሰት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳደሩን የገዳሙ ዋና አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ ጽጌሥላሴ መዝገቡ ከማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን ጋር በነበራቸው ቆይታ ገለጡ፡፡

ጦርነቱ በተለይ በላሊበላና አካባቢው ለአምስት ወራት በቆየበት ወቅት የገዳሙ የቱሪስት ፍሰት መቆሙን የገለጡት ዋና አስተዳዳሪው በዚህ ምክንያትም ከአንድ ሺህ በላይ የገዳሙ አገልጋዮች፣በገዳሙ ሥር ይተዳደሩ የነበሩ ሌሎች ገዳማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት፣ አዳሪ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና ገዳሙ ያስተዳድረው የነበረ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በገንዘብና በግብዐት እጥረት ምክንያት አደጋ ላይ እንደወደቁ ተናግረዋል፡፡

የላሊበላ ገዳምና አካባቢው ከሐምሌ ፳፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ጀምሮ ከትግራይ በመጡ ታጣቂዎች ቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ አገልጋዮችና ምእመናን አካባቢያቸውንና ቅርሶቻቸውን ጥለው እንዳይሰደዱ የማድረግ ሥራ ሲሠሩ መቆታቸውን የገለጡት ዋና አስተዳዳሪው ለቅርሶቹ ደኅንነት ሲባልም የትግራይ ታጣቂዎችና የመንግሥት ኃይሎች ጦርነቱን ከቅርሶቹ አካባቢ ርቀው እንዲያካሂዱ መምከራቸውንም አስታውቀዋል፡፡

ዋና አስተዳደሪው አያይዘውም በጦርነቱ ወቅት አንዳንድ የመንግሥት አካላትና ባለሀብቶች አካባቢያቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን አብዛኛው ምእመን ግን ቤተ ክርስቲያኑንና ቅርሱን ሲጠብቅ መቆየቱን አንሥተው ታጣቂ ቡድኑ በላሊበላ ከተማ የቆየባቸው አምስት ወራቶች ለቤተ ክርስቲያን፣ ለምእመናንና ለአገልጋዮች በርካታ ረጅም የሥቃይ ጊዜዎች ሁነው አልፈዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በጦርነቱ ወቅት የመንግሥትና የግል አገልግሎት መሥጫ ተቋማት ከጥቅም ውጭ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ የማኅበራዊ አገልግሎት መሥጫ ተቋም በመሆን ስታገለግል መቆየቷንም ያስረዱት አስተዳደሪው በጦርነቱ መካካል በተቻለ መጠን ቅርሶች እንዳይጎዱና የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ የመጠበቅና በአባታዊ ትእዛዝ የመከላከል ሥራ ሲሰሩ መቆየታቸውን አስረድተዋል፡፡ በገጠር አካባቢ ያለችው ቤተ ክርስቲያንም ጉዳት እንዳይደርስባት በአካባቢው ላሉ አገልጋዮችና ምእመናን ደብዳቤ በመጻፍ ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ የማድረግ ሥራ መሠራቱንም አክለዋል፡፡

በመጨረሻም ከቱሪዝም ፍሰቱ የሚገኘው ገቢ በመጥፋቱ በቤተ ክርስቲያን ሥር ያሉ ተቋማት ሁሉ ለከፋ ችግር መዳረጋቸውን የተናገሩት አስተዳደሪው ይህንን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ከፊታችን በድምቀት የሚከበረውን የ፳፻፲፬ ዓ/ም የልደት በዓልን ምክንያት በማድረግ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚመጡ ምእመናን በቻሉት ሁሉ ገዳሙን እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# መንበረ ጵጵስናቸው የማኅበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ማእከል ሆኖ መቆየቱ ተነገረ

ምኒልክ ብርሃኑ



ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ

የሰሜን ወሎ እና በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን የከሚሴ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሠተው ጦርነት ለአምስት ወራት ተወራ የነበረችው ወልዲያ ከተማ ነጻ መውጣቷን ተከትሎ ከማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን ጋር በነበራቸው ቆይታ መንበረ ጵጵስናቸው ደብረ ገሊላ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የድጋፍ፣ ርዳታና የሌሎች ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ማእከል ሆኖ መቆየቱን ተናገሩ፡፡

ኅብረተሰቡን በማስተባበር እና በብድር መልክ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ በመሰብሰብ እጅግ በጣም ለተቸገሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደለገሱ የገለጹት ብፁዕነታቸው ቤተ ክርስቲያኗ እንደ ርዳታ መስጫ ማእከል ሆና ሕዝቡ ያለውን እያመጣ ይሰጥ እንደ ነበር ገልጠዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አምስት ወራት ወልዲያ ከተማ የነበረችበትን ሁኔታ ለጣቢያው ሲያስረዱ "እግዚአብሔር ያንን የጨለማ ሰዓት ከሚያልፉ ሰዎች መካከል አትርፎ ታሪክ እንድናገር አድርጎኛል፡፡ እነዚያ አምስት ወራት ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ተለይተን የቆየንባቸው፤ የሚበላ፣ የሚጠጣ ያልነበረባቸው፤ በቋሚነት መድኃኒት ሲጠቀሙ የነበሩ ሰዎች መድኃኒት አጥተው የተሠቃዩባቸው እጅግ በጣም አስቸጋሪ ጊዜያት ነበሩ ብለዋል፡፡

አያይዘውም "ጦርነቱ የወለዳቸው በርካታ ችግሮች ቢኖሩም አገራችን ኢትዮጵያ የአየር ንብረቷ ምግብ ሆኖ አብዛኛውን ሰው አቆይቶናል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥም የዓለም አቀፍም ይሁን የሀገር ውስጥ ርዳታ ስላልገባ የተቸገርነው ምግብ ብቻ አልነበረም፤ መድኃኒቶችንም ጭምር እንጂ፡፡ ነገር ግን ድጋፍ እንዲያደርጉ በጠየቅነው መሠረት ለሦስት ወራት መድኃኒት ገዝተው የያዙ ወገኖች እየቀነሱ ለሌላቸው አከፋፍለናል" ብለዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አክለውም መድኃኒቱ ቢገኝም መውሰጃ ምግብ ያጥር እንደነበር፤ የመድኃኒቱ ዓይነትም እንደሚጠፋና እንደማይበቃ፤ ገጠሩም ከተማውም የጦርነት ቀጠና በመሆኑ ብዙ ሰው በረኀብ፣ በውኃ ጥም እና በመድኃኒት እጥረት እንዳለፈ ከጣቢያው ጋር በነበራቸው ቃለ መጠይቅ አስረድተዋል፡፡

በመጨረሻም ብፁዕነታቸው "የሰላም ዋጋው ብዙ በመሆኑ ሰላም ሲጠፋ ብዙ ነገር ይጠፋል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን መከራ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ዳግም አያምጣብን" ሲሉ አምላካቸውን ተማጽነዋል፡፡ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ የሰሜን ወሎ ዞን ዋና ከተማ ወልዲያ በታጣቂዎች ከመወረሯ በፊት ለሥራ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት በዝግጅት ላይ የነበሩ ቢሆንም "ምእመናን ወገኖቼን ትቼ መሄድ የሚያስችል ምንም ሞራል የለኝም" በማለት የመከራውን ዘመን ከሕዝብ ጋር እንዳሳለፉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ‹‹ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው››

የሐ.ሥራ ፳፥፴፭

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት ብዙ ወገኖቻችን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ ተገድለዋል፤በጠቅላላ ሃይማኖታዊ ና ማኅበራዊ ሕልውናቸው ሁሉ ለከፋ ችግርም ተዳርጓል፤ አብያተ ክርስቲያናትም ተዘርፈዋል ይህ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በሚበዙበት አካባቢ የደረሰው ውድመት የአብያተ ክርስቲያናት መዘረፍ በሀገር ላይ ያደረሰው ቀውስ ከባድ ሲሆን ቤተ ክርስቲያንንም ደግሞ ይበልጥ የጥቃቱ ሰለባ አድርጓታል፤ ዛሬም እያደረጋት ይገኛል።ጉዳቱ ከሞት፣ ከመፈናቀልና ከመሰደድም በላይ በሕይወት በተረፈው ኅብረተሰብ ላይ እየደረሰ ያለው ረኀብና እርዛት ልብ ይሰብራል ኅሊናን ያቆስላል።በየመገናኛ ብዙኃኑ እና በየማኅበራዊ ሚዲያውም በየቀኑ የሚሰማው የሰው ልጅ ሰቆቃ ልብ ድረስ ዘልቆ ይሰማል።

ቁም ነገሩ በየቀኑ የሚደርሰውን መፈናቀል፣ መሞት እና ስደት ሰምቶ ከንፈር ከመምጠጥ እና ከማዘን ባሻገር በተግባር የተገለጠ ክርስትና የሚጠበቅበት ጊዜ ነው።በመጽሐፍ ‹‹ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው›› እንደተባለ በጦርነቱ ቤትና ንብረት አልባ የሆኑትን ወገኖች መልሶ በማቋቋም ወደ ቀደመ ኑሯቸው እንዲመለሱ የማድረግ ኃላፊነት የሁሉም ክርስቲያን ግዴታ ሊሆን ይገባል።በአንጻራዊ ሰላም ውስጥ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል የሰላም እጦት ለሚያንገላታው ወገኑ በመድረስ አለኝታውን የሚገልጽበት ከጎኑ የሚቆምበት ጊዜ ነውና ሁሉም ልብ ሊል ይገባል።

በመሠረቱ ጦርነት ዘር፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ ቀለም እና ሃይማኖት ሳይለይ የሚያወድም፤ የሚያጠፋ መርዝ ነው።ሀገራችንም ዛሬ እያስተናገደች ባለችው ጦርነት ውስጥ ብዙ ንፁሑን ሰለባ ሆነዋል።በመሆኑም ያዘኑ ሊጽናኑ፤ ልባቸው የተሰበረ ሊጠገኑ፤ የሚችሉት በቅድሚያ ክርስቲያኖች ከጎናቸው መሆናችንን ስናሳያቸው ነው።ያዘኑትን በቃለ እግዚአብሔር በማጽናናት፣ የተቸገሩትን በመርዳት እና በተቻለ መጠን ሰላማዊ ኑሮን እንዲመሩ በማድረግ የወንጌሉን ቃል መፈጸም ከሁላችን ይጠበቃል።ምክንያቱም ወገንን መርዳት ከተወሰኑ አካላት፣ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ከእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚጠበቅ ነውና፡ ከሚበላውና ከሚለብሰው ከፍሎ ለመስጠት እጁን የሚዘረጋ፣ የሚያዝኑትን ለማጽናናት ከጎናቸው የሚቆም፣ ቤት አልባዎችን የሚያስጠጋ የተማረውን በተግባር የሚገልጥ ጠንካራ ክርስቲያን በመሆን ሰዎችን ማትረፍ ይጠበቅብናል።

እንደ ክርስቲያንም የሰው ሞት፣ ስደት እና መፈናቀል በራሳችን ላይ እንደተደረገ ልንገነዘብ ይገባል፤ ያኔ ማንንም ከማንም ሳንለይ እጆቻችንን ለእርዳታ መዘርጋት እንችላለንና፤ ዛሬ ያልረዳነውን ፤ ያልታደግነውን ክርስቲያን ነገ ልናገኘው አንችልምና ቀን ሳለ መሠራት ያለብንን መሥራት ከእኛ ይጠበቃል።የታረዙትን በማልበስ፣ የተራቡትን በማብላት፣ ያዘኑትን በቃለ እግዚአብሔር በማጽናናት የተበተኑትን የቤተ ክርስቲያን መንጋዎች መሰብሰብ የቤተ ክርስቲያን እና የክርስቲያኖች ዐቢይ ሥራ ሊሆን ይገባል።ቤተ ክርስቲያንም ምእመናን የተጎዱ ወገኖቻቸውን በመርዳት ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን ይወጡ ዘንድ ከመቼውም ጊዜ በላይ መምከር፣ ማስተማር እና መመሪያ መስጠት ይጠበቅባታል።

ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናትም ተሰደዋል፣ መገልገያ የሆኑት ንዋያተ ቅዱሳት ተዘርፈዋል ባዶዋንም ቀርታለች፣ እንዳልነበረች ሆናም በጦርነቱ ወድማለች።ቤተ ክርስቲያንም አንዲት ናትና በውድምቱ ቦታ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ልናደርግ ይገባል፤ ካህናት አገልጋዮቿ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ተግቶ መሥራትም የክርስቲያኖች ኃላፊነትም ግዴታም

ጭምር ነው።የተዘረፉ ንዋያተ ቅድሳቷን በመተካት እና በማሟላት ቤተ ክርስቲያን የዕለት ከዕለት መንፈሳዊ አገልግሎቷን እንድትቀጥል ማድረግ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። የፈረሰውን ለመጠገን ወደ ቀድሞ ለመመለስ እንደ ነህምያ ተጠራርቶ በአንድ መቆም ወቅቱ የሚጠይቀው ዐቢይ የክርስትና ጉዳይ ነው።

ሌላው በውድመቱ ቦታ የተሰማውና የታየው  በሌውም እንዳይሆን ተግቶ ከመጸለይ ጎን ለጎን ለተጎዱ ወገኖች እና ለአብያተ ክርስቲያናት መድረስ ቀጠሮ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን ተገንዝቦ ዛሬ ላይ አጥብቆ መሥራት የሁላችን ኀላፊነት ሊሆን ይገባል። ሕዝበ ክርስቲያኑ ተረባርበን የክርስቲያኖችን ሕይወት መታደግ፣ የአብያተ ክርስቲያናትን አገልግሎት ማስቀጠል ይኖርብናል። የተዘጉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ዳግም ተከፍተው የተበተኑ ተማሪዎች ተሰባስበው የአብነት ትምህርት ቤቱ አገልግሎት እንዲቀጥል ለማድረግም ገና ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል፤ የፈረሱት ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲውሉ ከእኛ ሌላ ማንም የለምና አለኝታነታችንን በተግባር መግለጥ ተገቢ ነው፤ የቤተ ክርስቲያንም ጉዳይ የእያንዳንዱ ክርስቲያን ጉዳይ ነውና በዚያ ልክ ማሰብ፣ መሥራት፣ መተባበር ከእኛ ይጠበቃል። የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ልጆቻቸውን በማጽናናት፣ በማስተማር እና በማገዝ እንዲጸኑ ማድረግ፤ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች ወደ ቀድሞ ሕልውናቸው ተመልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ ባማድረግ ያላቸውን መዋቅር ሁሉ ሊጠቀሙ ይገባል እንላለን።

በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉዳቷ ብዙ ነውና ሁላችንም አጥብቀን ልናስብበት ይገባል። በጦርነቱ ይበልጥ የተጎዱት አብያተ ክርስቲያናትና ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መሆኑን በውል ተገንዝቦ ማንንም ከማንም ሳንለይ በየትኛውም ቦታ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የምትጠገንበትን መንገድ መፈለግ ተገቢ ነው። የፈረሰችው ቤተ ክርስቲያን የሚጠግናት ሰው ያስፈልጋታልና ሕዝበ ክርስቲያኑ ተረባርቦ ይህን መሥራት ይጠበቅበታል።የእርዳታ እጆቻችንን በመዘርጋት ለተፈናቀሉት ምእመናንና ለወደሙት አብያተ ክርስቲያናት እንድረስላቸው፤ የቻልነውን በመስጠትና በመርዳት እንታደጋቸው።

# ሐሰተኞች አጥማቂዎች የቤተ ክርስቲያናችንና የምእመናን ፈተናዎች

• ስለጥምቀት ቤተ ክርስቲያን ምን ታስተምራለች? መጻሕፍትስ ምን ይመሰክራሉ?

**ክፍል ሦስት**

ሻምበል ጥላሁን

### አጥማቂስ ማን?

የተወደዳችሁ አንባብያን ከዚህ በፊት በነበሩት ሁለት እትሞች ላይ ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት ተከታታይ ጽሑፎችን ማቅረባችን ይታወሳል። ሦስተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦

መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ አዝናው በአዲስ አበባ ሀገረስብከት የቱሉዲምቱ ቅዱስ ጊዮርጊስና ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል ኃላፊ ናቸው። ቀሲስ ምንአለ ስለ ሐሰተኛ አጥማቂያን ሲናገሩ "የልዑል እግዚአብሔር ቸርነትና አዳኝነት ከሚገለጥባቸው ምክንያቶች ወይም መንገዶች አንዱ ጠበል ነው። በገዳማትና አድባራት ቅጽር፣ በቅጽሩ ዙርያና በአካባቢው ሰበካዎች ባሉ የጠበል ቦታዎች በፍጹም እምነት የሚቀርቡ ምእመናን በጠበል እየተጠመቁ ፈውስ ያገኛሉ፤ የእግዚአብሔር ደገኛ ተኣምራት እየተገለጸ ምሕረቱ የተደረገላቸው ሁሉ በየጊዜው ድንቅ ሥራውን እየመሰከሩ ይገኛሉ። "ይላሉ።

መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ ስለ ሐሳውያኑ እንደሚናገሩት፤ ከቅዱስ ሲኖዶስ ዕውቅና ውጭ ከፋብሪካ የተመረተና በካህናት ለዚህ አገልግሎት ያልከበረ ዘይት ‹‹ቅብዐ ቅዱስ ነው›› በማለት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዐጸድ ውስጥ በማከፋፈልና በመሸጥ ቤተ ክርስቲያንን የንግድ ማእከል አድርገዋታል ቀሲስ ምንአለ። በሐሳውያኑ አጥማቂዎች ፈውስ ሁሉ የሚከናወነው በጩኸት ነው። ጩኸት ከሌለ ፈውስ የለም ብለው ያምናሉ ይላሉ።

በነዚህ ሐሳውያን ዘንድ አጋንንት ያልጮኸለት ሰው ገና የፈውሱ ጊዜ እንዳልደረሰና በእርሱ ላይ ርኩስ መንፈስ እንዳለበት፣ እንዲገለጥና እንዲወጣለት ራሱን በራሱ በመቁጠሪያ እንዲደበድብ ‹ትምህርት› ይሰጠዋል የሚሉት መምህሩ ። አካል ጉዳተኛው ሁሉ አጋንንት እንደያዘው ሰው እንዲጮህ ይደረጋል ሲሉ ያስረዳሉ። በነዚህ ሐሳውያን ዘንድ፤ ደዌ ዘዕሜት፣ ደዌ ዘአኮቴት ደዌ ዘኀጢአት የሚሉትን ለግንዛቤ ያህል እንኳ በውል ለይተው አያውቁም ይላሉ።

በተለያየ በሽታ ተይዘው መዳንን ሽተው የሚመጡ ሕሙማን ኃጢአታቸውን በዐደባባይ እንዲናዘዙ ያደርጋል የሚሉት ቀሲስ ምን አለ። እነዚህ ሐሳውያን የብዙ ሕዝበ ክርስቲያንን ገመናና ኃጢአት ሕሙማኑ ዐውቀውም ይሁን ሳያውቁ ገቢ ማስገኛ እንዲኾን በቪዲዮ አስቀርጸው በሲዲ ለገበያ እንደሚያውሉትም ይናገራሉ።

በሐሰተኞች አጥማቂዎች ‹‹ጠበል ብቻውን መጠመቅ ዋጋ የለውም፤ በመቁጠሪያ ራሳችኹን ካልደበደባችኹ›› በማለት ለምእመኑ ይናገራሉ የሚሉት ቀሲስ ምንአለ ‹‹ቅብዐ ቅዱስ ነው›› ብለው ከሚሸጡት የፋብሪካ ዘይት በተጨማሪ ተጠማቂው መቁጠሪያ እንዲገዛ እንደሚያስገድዱም ያስረዳሉ። እነዚህ አጥማቂዎች ነን ባዮቹም ምእመኑን ለማደናገር እነርሱ ከሚሸጡት መቁጠሪያ ውጭ ሌላው ዋጋ እንደሌለው እንደሚሰብኩም ይናገራሉ።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በዚህ ጉዳይ ላይ በአንዳንድ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ላይ ባደረገው ምልከታ የመዳን ተስፋ ይዘው ከየአህጉረ ስብከቱ ወደነዚህ ሐሳውያን አጥማቂዎች ሳያውቁ የሚመጡ ምእመናን መጠለያ አጥተው በመጉላላታቸው ለተጨማሪ በሽታ የተጋለጡ፣ በመቁጠርያ በመደብደባቸውና የፋብሪካ ዘይት ያለ አግባብ ጠጡ እየተባሉ በመገደዳቸው ለኀልፈት የተዳረጉ ሕሙማን መኖራቸውን የጽሑፉ አቅራቢ ከአካባቢው መእመናን ሰምቷል።

የአንዳንዶቹ "አጥማቂዎች" መኖርያ ቤት ሀብተ ፈውስ እንዳላቸው ደገኛ አባቶች በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ተጋድሎ ተወስኖ ሳይሆን በሚልዮን ብር ወጪ በተገነባ ቪላ እንደሚኖሩ የአደባባይ ሀቅ ነው።

እነዚህ ሐሰተኛ አጥማቂዎች ሰይጣንን እናስወጣለን የሚሉበት የ‹‹ፈውስ መንገድ›› አንዱ በፕሮቴስታንታዊ ዘይቤ ሕሙማንን በቦክስ እና በጥፊ በመማታት መሆኑንም የዘገባው አቅራቢ

በምልከታው ወቅት አረጋግጧል። የማጥመቁ መርሐ ግብር ሲጀመርም ሆነ ሲያበቃ በጸሎት ፈቃደ እግዚአብሔር ተጠይቆበት እንደማያውቅም ማረጋገጥ ተችሏል። በቤተክርስቲያናችን አባቶቻችን ሲያጠምቁ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ በቃለ እግዚአብሔር አጋንትን በማቃጠል፣ በቅዱስ መስቀል በመዳሰስ፣ ጠበል በመርጨት ዳግመኛ ወደ ሕሙሙ እንዳይደርስ በማድረግ እንደሆነም ቅዱሳት መጽሐፍት የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። (ሉቃ.፰÷፳፮-፴፫፤ ፪ኛነገ.፭÷፰-፲፱፤ ፩ኛቆሮ.፩÷፲፰)

ሐሰተኞቹ አጥማቂዎች ‹‹እኛ የምንጨነቀው ሰውን ለማዳን እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አይደለም፤›› በማለት በሰንበት ቀን ስግደት ያዛሉ፤ በቤት መቅደስ ሥርዐተ ጸሎት እየተካሄደ /ቅዳሴ እየተቀደሰ፣ ማኅሌት እየተቆመ፣ የደብሩ ክብረ በዓል እየተደረገ/ እነርሱ ሌላ መርሐ ግብር ያካሂዳሉ፣ በሽተኞች እንዲጮኹ፣ ዕልል እንዲሉ እንደሚያደርጉ አሠራራቸውን ለመከታተል በሄድንባቸው ቦታዎች ሁሉ ያየነው ሐቅ ነው።

ስለ ሐሰተኞቹ አጥማቂዎች በዘገባው አቅራቢ በተጠቀሱት ነጥቦች እንደሚስማሙ የሚናገሩት መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ፤በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ማንም ሰው በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ለግል ጥቅም የሚውል ምንም ዐይነት ንግድ ማካሄድ የለበትም ሲሉ ያስረዳሉ። ሐሰተኞቹ አጥማቂዎች ግን በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ለራሳቸው ገቢ ማስገኛ የሚውሉ ሌሎች ንግዶችን ሲነግዱ ይስተዋላል የሚሉት ቀሲስ ምንአለ፤በዚህም በአንድ ቀን ብቻ በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚሰበስቡም ያስታውሳሉ።

ከንግዱ ባሻገር ከጠበል አገልግሎት የሚገኘውና በስእለት፣ በስጦታ የሚሰበሰበው ገንዘብ በአግባቡ ለቤተ ክርስቲያን ገቢ መኾን ሲገባው ለአጥማቂ ነኝ ባዩቹ የሚሰጥበት አሠራር ማስተከላቸውንም ይናገራሉ።

ሐሰተኞቹ በሚያጠምቁባቸው አንዳንድ ቦታዎች ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን በምንመጣበት ጊዜ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የጠበቀ ልብስ መልበስ ቢገባንም ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዕውቀት የሌላቸው ሴቶች ሱሪ አድርገው፣ ጥፍር ቀለም ተቀብተው፣ ፀጉራቸውን በዊግ (ሰው ሠራሽ ፀጉር) ተሠርተው፣ … በነዚህ ቦታዎች ሲመጡ ርኲስ መንፈስ ያለባቸው ሰዎች እንዲህ ሆነሽ አትገቢም ብለው በድንጋይ ጭምር ሲደበድቡ የዘገባው አቅራቢ አይቷል። እንዲህ ሲደረግ ሲታይ ሰይጣንን በእግዚአብሔር ቤት ሥርዓት አስከባሪ ያደረገው ማን ነው? ተብለው ሲጠየቁ እመቤቴ፣ ሚካኤል፣ …መንፈሱን አዝዘውት ነው ይላሉ። ይህ አሠራር ሰይጣንስ ከቅዱሳን ጋር ምን ኅብረት አለው? እንድንል ያስገድደናል።

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡን ቀሲስ ምን አለ ‹‹ይህ አሠራር ፈጽሞ ስሕተት ነው። ሰይጣን በምንም ዓይነት ሁኔታ የእግዚአብሔር ቤት ሥርዓት አስከባሪና ሕግ አስጠባቂ ለመሆን አይችልም። ምክንያቱም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹… ጽድቅ ከአመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?› (፪ቆሮ ፮÷፲፬-፲፭)። ሲል አስተምሮናልና››ይላሉ ቀሲስ ምንአለ። መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ ‹‹ብዙዎቻችን ስለ ሰይጣን ባሕርይና ስለ እግዚአብሔር የፈውስ አሠራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት ስለሌለን እንሳሳታለን›› ሲሉም ያስረዳሉ። አያይዘውም በዘመኑ ያለው የፈውስ አሠራር የእግዚአብሔርን ክብር ከመግለጽ ይልቅ በአብዛኛው ሰይጣንን በማናዘዝ (ቃለ መጠይቅ በማድረግ)፣ እርሱን በማዳመጥና ሐሳቡን እንደ ትክክለኛ መልእክት በማስተላለፍ ላይ ያተኮረ እንደሆነም ይገልጻሉ።

ይህ ዓይነቱ አካሄድ አጥማቂዎች ነን የሚሉትን ሰዎች ተአምር አድራጊዎች አስመስሎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የስሕተት ትምህርት በማስተላለፍ ሰዎችን ለበለጠ እሥራት እየዳረገ ያለ ክፉ አሠራር ነው በማለት ቀሲስ ምንአለ ያስረዳሉ።

ቀሲስ ምናለ አክለውም ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹ይህም አያስደንቅም፤ ሰይጣን ራሱ ተለውጦ እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላልና ታላቅ ነገርም አይደለም፤ ፍጻሜያቸው ግን እንደሥራቸው ነው።›› (፪ኛቆሮ ፲፩፥፲፬–፲፭) ብሏልና ሰይጣን በሚናገረው ውስጥ ምንም ዓይነት መልካም ነገር እንደሌለ መረዳት ይገባናል የሚሉት መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ፤ መልእክተኞቹም ቅዱሳን መላእክትን ቢመስሉ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶች ከክርስቲያናዊ ሥርዓት ውጭ ሆነው ሲመጡ አስተምሮ ማስተካከል ሲገባ እንዲህ ሆነም አይገቡም፣ በዛሬው ዕለት አይሰገድም እያሉ ሰላማዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት (ቃለ እግዚአብሔር መስማትን፣ ጸሎትና ምህላን፣ ስግደትን፣ …) ሲረብሽ ታዞ ነው ተዉት ማለት የሰይጣን ተከታይ ከመሆን የተለየ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም ይላሉ ቀሲስ ምንአለ።

ሰይጣን ዓላማው እኛን የነፍሳችን ድኅነት ከሆነው ከጌታችን፣ ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መለየት ነውና በመንፈሳዊ ልብ ማስተዋል ይገባናል ሲሉ

የሚያስረዱት መጋቤ ሐዲስ ቀሲስ ምንአለ፤ እንዲህ ያለው የተሳሳተ አሠራር ከቤተ ክርስቲያናችን መነቀል አለበት ይላሉ።

መጋቤ ብሉይ ወሐዲስ አባ ገብረኪዳን ግርማ ሐሳውያኑን አስመልክተው በአንድ መድረክ ላይ ሲያስተምሩ ‹‹እነዚህ ሐሰተኞች አጥማቂዎች ሳኦላውያን ናቸው›› ብለው ከገልጿቸው በኋላ ‹‹ሳኦል በሌለው ሥልጣነ ክህነት ሳሙኤል እስኪመጣ መታገሥ አቅቶት መሥዋት በማቅረቡ የተቀበለውን ቅጣት እናውቃለን። እነዚህ ሳኦላውያን አጥማቂዎች ክህነት አላችሁ ሲባሉ እንደሌላቸው ይናገራሉ›› ያሉት አባ ገብረኪዳን ‹‹ታዲያ በምን ሥልጣን ታጠምቃላችሁ ሲባሉ እግዚአብሔር መርጦኝ ነው ይላሉ› በማለት አስተምረዋል።

ከዚሁ አያይዘውም ‹‹ተአምርና ሕግ መለየት አለበት። በተአምር እያመካኙ ምስኪኑን ምእመን መጫወቻ እያደረጉት ይገኛሉና ቤተ ክህነት እነዚህን ሰዎች በሕግ ለመጠየቅ መዘግየት የለበትም›› ሲሉ አስተምረዋል።

ቤተ ክርስቲያን ስለ ጥምቀት ምን ታሳ,ስተምራለች? መጻሕፍትስ ምን ይመሰክራሉ? የሚለውን ስንመለከት በሥርዓተ ቤተክርስቲያንም ሆነ በገድለ ቅዱሳን ውስጥ ቅዱሳን በገዳማዊ ሕይወት፣ በሰማዕትነት፣ በክህነት አገልግሎት ሲሠማሩ እግዚአብሔር ምእመናንን ለማጥቀም ወይም ክብረ ቅዱሳንን ለመግለጥ በእነርሱ ላይ ተአምራትን ያደርጋል። እነርሱ ግን ይህ ክብር እንዳይገለጥባቸው ሲሸሹ፣ እኔ አላደረግኩም ሲሉ ወይም ስለራሳቸው ደካማነት ሲነገሩ እናያለን እንጂ ‹ኑ እንፈውሳችኋለን› ብለው ዐዋጅ ሲናገሩ በሥርዓተ ቤተክርስቲያንም ሆነ በገድለ ቅዱሳን አንብበንም አናውቅም።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በገዳማዊ ሕይወት፣ በክህነት አገልግሎት፣ የጸሎት ሕይወት ወይም ሌላ አንዳች ተጋድሎ ሳይኖረው ማጥመቅ ብቻ ሥራው የነበረ ክርስቲያን የለም። ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው አባቶችና እናቶች የሌላው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ውጤት ወይም ነጸብራቅ ነበር እንጂ ሥራቸው እየዞሩ ማጥመቅ እንዳልነበረ ገድላት ድርሳናቱ ያስረዳሉ። የሐዋርያት ሥራን ብናነብ ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት ሲሠማሩ በአንድ በኩል አሕዛብን ወደ ክርስቶስ ለመጥራት በሌላ በኩል የአንደበት ትምህርታቸውን በእጃቸው ተአምር ለማጽናት ተአምራትን ያደርጉ ነበር እንጂ በአንድ ከተማ ውስጥ ሲያጠመቁ ውለው ያደሩበት፣ ወይም ከወንጌል አገልግሎት ተለይተው አጥማቂ ብቻ የሆኑበት፣ ወይም ደግሞ በዚህ ቦታ ፈውስ እንሰጣለንና ተሰብሰቡ ብለው ያስነገሩበት አንድም ማስረጃ የለም። በገድለ ቅዱሳንም ቅዱሳን ጸጋ እግዚአብሔር ሲያድርባቸው፣ ሥጋቸውንና ሰይጣንን ድል ሲነሡ፣ በክርስትናቸው ሲጸኑ ተአምራት ይከተሏቸዋል እንጂ እንዲሁ ማጥመቅና መፈወስ ብቻ ሕይወቱ የነበረ ቅዱስ የለም። ሰው ያለ ተጋድሎ ጸጋ አያገኝምና።

ይሁን እንጂ በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ማጥመቅ የሚችለው የቅስና ሥልጣነ ክህነት ያለው ብቻ ነው። ቅስና የሌለው ሰው አያጠምቅም፤ አይናዝዝም፤ አይባርክም (ፍት.ነ.ፍ.መ.አን.፫ ቁ.፷፩) ቅዱሱን ቅባት መቀባት የሚችለው የክህነት ሥልጣን ያለው ብቻ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። (ያዕ.፭÷፲፬) ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በገንዘብ አይሸጥምና አጥማቂው ካህን መማለጃ መቀበል አይገባውም። (ፍ.መ.አን.፯)

ነፍስ ኄር ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ በ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት ባሳተሙት ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በሚናገረው መጽሐፋቸው ገጽ ፷፱ ላይ የሥልጠነ ክህነትን ተግባር እንዲህ ዘርዝረዋል፦ "ክህነት እግዚአብሔርና ሰውን ማገልገል ነው። እግዚአብሔርን ማገልገል ማለት ካህናት መላእክትን መስለው በመዓልትና በሌሊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው። ሰውን ማገልገል ማለትም ማጥመቅ፣ ማቊረብ፣መባረክ፣መናዘዝ፣በሞት ለሚለዩ ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ፤ በጠቅላላው በትምህርት፣ በትሩፋት ክርስቶስን መስሎ አብነት ሆኖ መገኘት ነው።" ይላሉ።

በእነዚህ ሐሳውያን አጥማቂዎች ላይ አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክህነቱም በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱም እነርሱን የሚያወግዙ ርምጃዎች ቢወሰዱም፤ የሚወሰዱት ርምጃዎች ዘላቂ ባለመሆናቸው አሁንም እነዚህ እኵያን በየደብሩና በየጉራንጉሩ ይህን የአጋንት ሥራ ሲከውኑት ይታያሉ።

# “የዘርና ገንዘብ ፍቅርን የናቁ፣ በምእመናን እምነትና ፍቅርን ያገኙ፣ የወንጌል አርበኛና የማሕሌት ቀንዲል ነበሩ”


ካሳሁን ለምለሙ

**ክፍል አንድ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን የሊቃውንት መፍለቂያ፣የግብረ ገብነት መነሻ፣የሥርዓተ ትምህርት መነሻ፣ እንዲሁም የመልካም ዕሤት ባለቤትም ናት:: ቤተ ክርስቲያናችን አያሌ ሊቃውንትን ያፈራችና የምታፈራ በመሆኗ ለልጆቿ የምትሰጠው ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ መግቦት ሳይቋረጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል:: ትውልዱም በሥነ ምግባር የታነጸ እንዲሆን፣ በአብነትና በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ትምህርቶችን ጠንቅቆ እንዲያውቅ ከማድረግ አኳያ የሊቃውት አባቶቻችን ድርሻ የላቀ ነው::

ዕድሜ ዘመናቸውን ቤተ ክርስቲያንና ትውልድ እንዲቀጥሉ ያላሠለሰ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ አባቶቻችን በርካቶች ናቸው:: በቤተ መቅደስ ካለው አገልግሎት በተጨማሪ ወንበር ዘርግተው፤ ተማሪዎችን ሰብስበው፤ የሚያስተምሩና እያስተማሩ ያሉ አባቶቻችን ባልተመቻቸላቸው ሁኔታ ውስጥ ሆነው ምን ያህል ዋጋ እንደከፈሉና እየከፈሉ እንደሆነ መረዳት ቀላል ነው:: እስከ ዕረፍተ ዘመናቸው ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ያለድካም ሲያገለግሉ ከቆዩ አባቶች መካከል መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ አንዱ ናቸው:: አባታችን መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ በዕረፍተ ዘመን እስከተገቱበት ጊዜ ድረስ ገጠር፣ከተማ፣ቆላና ደጋ እንዲሁም ምቾትን ሳይፈልጉ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ የነበሩ የወንጌል አርበኛና የቤተ ክርስቲያን ጠበቃ ነበሩ:: ስለሆነም አባታችንን የዚህ እትም የቤተ አብርሃም ዐምድ እንግዳችን አድርገናቸዋል:: መልካም ንባብ::

መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ ከአባታቸው ከቄስ ስሜነህ ጀምበር እና ከእናታቸው እማሆይ ጉዳይ ተበጀ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም በጎጃም ክፍለ ሀገር በአገው ምድር አውራጃ ዳንግላ ወረዳ ልዩ ስሙ ማንጉዳ ማርያም ተወለዱ:: እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በትውልድ ሥፍራቸው ከታዋቂው የድጓ መምህር ከየኔታ ምሕረት ወንድም ዘንድ ከፊደል እስከ ጾዋትወ ዜማ ተምረው ከቀድሞ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ዘንድ የዲቁና ማዕረግ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ተቀብለዋል:: በመቀጠልም በዳንግላ ወረዳ ከመሪጌታ ክነፈ ርግብ ዋስታ ጊዮርጊስ ቅኔ ተምረዋል፤ በደምበጫ ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም ከታዋቂው ሊቅ ከመሪጌታ ብዙአየሁ አስጌ ቅኔ ከነአገባቡ፣ ሰዋስው ከነአመሉ ጠንቅቀው ተምረዋል:: መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ እንደገናም ወደ ትውልድ ሥፍራቸው በመመለስ እንዲሁ ከየኔታ ምሕረት ወንድም ዘንድ ድጓ ተምረው አጠናቀዋል:: መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ በ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ሰዓቲ ባለእግዚአብሔር ከሚገኙት መሪጌታ ኤፍሬም ዘንድ አቋቋም የተማሩ ሲሆን ለአቋቋም ትምህርት ሙያ የነበራቸው ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ ስለነበረ በድኩሊ ሚካኤል ከርእሰ ደብር መዝገቡ ያዛቸው ከመሪጌታ ዓይነ ኩሉ በማንጉዳ ተክለ ሃይማኖት፣ በአዴት ፍልሰታ ደብር ከመሪጌታ ዘለዓለም ያየህ፣ በዳንግላ



መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ

ከታወቁት ሊቅ ከየኔታ ሐዋዝ አፈ ወርቅ ለመምህርነት በሚያበቃ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሄድ በወቅቱ ከነበሩት ታላቁ ሊቅ መጋቤ አዕላፍ የኔታ ሔኖክ ወ/ሚካኤል ዘንድ በአቋቋም መምህርነት ተመርቀዋል:: በተጨማሪም በ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ወደ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት በመግባት ለአራት ዓመታት ያህል የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን በትጋት ተከታትለው በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቀዋል:: ከመንፈሳዊ ትምህርታቸው ጎን ለጎንም ዘመናዊ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል:: ከዚህ

ባሻገር በቅድስት ሥላሴ መንሳዊ ዩኒቨርስቲ ለአምስት ዓመታት የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው በ፲፱፻፲፫ ዓ.ም ድግሪያቸውን ካገኙ በኋላ የማስተርስ ትምህርታቸውን ለመቀጠል በዝግጅት ላይ ነበሩ፡፡

በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የቅስና ማዕረግ ከተቀበሉ በኋላ በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ወደ ባሌ ሀገረ ስብከት ሄደው በዶዶላ ገ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለሁለት ዓመታት በመሪጌትነትና በስብከተ ወንጌል አገልግለዋል፡፡ ከዶዶላ ከተመለሱ በኋላም ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ በጎጃም ክፍለ ሀገር የአገው ምድር አውራጃ ሊቀ ካህናት ሆነው ለሦስት ዓመታት አገልግለዋል፡፡

በተጨማሪም ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኘው የመካነ ቅዱሳን ኢያቄም ወሐና ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም ከ፲፱፻፹፰ ዓ.ም እስከ ፳፻ ዓ.ም በመርካቶ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በደብሩ ስብከተ ወንጌልን ከመስፋፋታቸው በተጨማሪ ደብሩ አሁን ላለበት ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በዚሁ ቆይታቸው የደብሩ ዋና አስተዳዳሪና የልማት መሪ ከነበሩት አባታችን ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ጋር በመሆን ምንም እንኳን የሥራ ምድባቸው የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ቢሆኑም በማሕሌቱ መሪጌታ፣ በቤተ መቅደሱ ካህን፣ በልማቱ ቀያሽ መሐንዲስ፣ የኢኮኖሚ እጥረት ሲያጋጥም አለኝታና አስተባባሪ በመሆን ሙሉ ሕይወታቸውን ሰጥተው በማገልገል ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ይህው አገልግሎታቸው ለከፍተኛ ኃላፊነት ስላሳጫቸው በ፳፻ ዓ.ም በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል አቅራቢነት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ በመዝገበ ምሕረት ቅዱስ ፋኑኤል ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ ሆነው ተሹመዋል፡፡ በወቅቱም አሁን በደብሩ አገልግሎት እየሰጠ የሚኘውን ካቴድራል በማሠራት የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡ በ፳፻፪ዓ.ም ወደ ደብረ ይድራስ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያ በተሰጣቸው ዋና አስተዳደሪነት ተዛውረው በዚሁ ደብር ያሠሩት የልማት ሥራ ለመንፈሳዊ አገልግሎቱ ስኬታማነት አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ ለደብሩ የሚያግዙ ንዋያተ ቅድሳት እንዲገዙና እንዲሟላለትም በማድረግ የሚጠበቅባቸውን የዋና አስተዳደሪነት ድርሻ በሚገባ ተወጥተዋል፡፡ ከዚያም ወደ ደብረ ምሕረት ኮቴቤ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል በመዛወር ለደብሩ ቋሚ የገቢ ምንጭ በመፍጠር፣ የአገልጋዩን ኑሮ በማሻሻል፣ ዘመናዊ ትምህርት ቤቱን በማስፋፋት፣ ቅጽረ ግቢው ላይ ሴራሚክ በማስነጠፍ እንዲሁም ዘመናዊ ፋውንቴን በማሠራት ሰፊ አገልግሎት ፈጽመዋል፡፡ ካቴድራሉ የነበረበትን የመብራት ችግር በዘመናዊ ጄኔሬተር በመተካት ዘርፈ ብዙ የካቴድራሉን ችግሮች ለመቅረፍ ተጣጥረው ተሳክቶላቸዋል፡፡

ሌላው በ፳፻፲፩ ዓ.ም የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ውስብስብ የሆነ ችግር በገጠማት ወቅት፣ ሕዝበ ክርስቲያኑም ለከፋ ብሶትና እንግልት ተጋላጭ በሆነበት ጊዜ መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ለችግሩ መፍትሔ ሰጭ፣ የተጣላ አስታራቂ ባለሙያ እና የትሕትና አባት መሆናቸው ታምኖበት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ መልካም ፈቃድ ወደ አየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል በአስተዳዳሪነት ተዛውረዋል፡፡ በተሾሙ ማግስት በደብሩ የነበረውን ችግር ለመፍታት ያመቻቸው ዘንድ ችግሮቹን የውስጥና የውጭ ብሎ በመለየት ዘላቂ መፍትሔ አምጥተዋል፡፡ እርሳቸው ያደረጉት ጥረት የተራራቁትን አቀራርቧል፣ ሰላም በጠፋባቸው አካላት መካከል ሰላም እንዲወርድ አድርጓል፤ በዚህም ባገለገሉባቸው ጊዜያት ሁሉ የሰላም አባትነታቸውን በሥራ አስመስክረዋል፤ በደብሩ ሁሉን አቀፍ ዕርቅና ሰላም በማስፈናቸው ምክንያት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ርቀው የነበሩ ምእመናን ልጆቻቸውን ወደ ዐውደ ምሕረት እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡

መደበኛና ልዩ ጉባኤያትንም በየደረጃው በማዘጋጀት በሕዝበ ክርስቲኑ መካከል ተዘርቶ የነበረውን የጥላቻና የመጠላለፍ መንፈስ በወንጌል ትምህርት አረስርሰው ወደ ቀደመ ሰላሙ እንዲመለስ አድርገዋል፡፡ የደብሩን የልማት ኮሚቴ በማጠናከርም የደብሩን ገቢ የማስዋብ ሥራ ካጠናቀቁ በኋላ የተጀመሩ የውስጥና የውጭ ሥራዎችም በመሥራት ለደብሩ ይዞታ በመስጠታቸው ከሰማንያ አራት ሽህ ስድስት መቶ ካሬ ሜትር በላይ ይዞታ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲካተት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ለካህናት ኑሮ መሻሻል ከነበራቸው ቁርጠኛ አቋም በመነሳት የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ካህናትና ሠራተኞች ደመወዝ እንዲሻሻል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ሰበካ ጉባኤንና ልማት ኮሚቴን አጠናክረው ሰንበት ትምህርት ቤቱን አደራጅተው በፍቅርና በሰላም በመምራት እስከ

የካቲት ፲፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ለሁለት ዓመታት በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት አገልግለዋል። ከ፳፻፲፫ ዓ/ም የካቲት ወር ጀምሮ በሞተ ሥጋ እስከተለዩበት መስከረም ፴ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ድረስ በምዕራፈ ጻድቃን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ካቴድራል ተዛውረው አገልግለዋል። በአገልግሎት ቆይታቸውም የተለያዩ ሽልማቶችና የዕውቅና የምስክር ወረቀቶችን አግኝተዋል።


በአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል በሥራ ላይ እያሉ ላመጡት ሰላምና ፍቅር ካህናትና ሠራተኞች የአንገት ወርቅ፣ ፈረጅያና የብር የእጅ መስቀል፣ ሙሉ መቀደሻ ልብሰ ተክህኖ ከብር የአንገት መስቀል ጋር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ የአገልግሎት ቦታቸው ብዙ ጊዜ በአዲስ አበባ ላይ ቢሆንም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በገጠር ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መቀደሻ አልባሳትና የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳትን በስፋት ያበረከቱ ሲሆን በተለይ ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ለሚገኙት ማንጉዳ ቅዱስ ሚካኤልና ማንጉዳ ቅድስት ማርያም አብያተ ክርስቲያናትን ሙሉ የክዳን ቆርቆሮ በመለገስ አሠርተዋል። የቀለም ቀንዱ ክቡር መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ የሰላምና የፍቅር አባት፣ ትሑት ስብእና የነበራቸውና በተአምኖ እግዚአብሔር የሚታወቁ የክህነት አርማ የሆኑ አባት ነበሩ።

መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ከወይዘሮ መሰለች ጌታሁን ጋር በትውልድ ቦታቸው በማንጉዳ ማርያም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጋብቻቸውን ፈጽመው ሦስት ወንድና አንድ ሴት በድምሩ አራት ልጆችን አፍርተዋል። መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ አገልግሎት ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው ድንገተኛ ሕመም ምክንያት በተወለዱ በ፶፫ ዓመታቸው መስከረም ፴ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም ተለይተዋል። ዜና ዕረፍታቸው ከተሰማበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ አበባ በሚገኙ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ልዩ ልዩ አገልጋዮች እንዲሁም የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራልና የምዕራፈ ጻድቃን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ካቴድራል አገልጋዮች ጸሎተ ፍትሐት አድርገዋል። ከብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የአዲስ አበባና ጉራጌ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ጀምሮ፣ ብፁዕነ አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የየመምሪያ ኀላፊዎች፣ ከገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ የጽ/ቤት ሠራተኞች፣ የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርቲያን አገልጋዮች፣ ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተወጣጡ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ጋር በርካታ ምእመናንና ምእመናት፣ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት ጥምቀት ፩ ቀን ፳፻፲፬ዓ.ም አገልግሎት ይሰጡበት በነበረው በአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈጽሟል።

የመልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ በዕረፍት ዘመን መገታታቸውን አስመልክቶ የአየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካህናትና ምእመናን በምስክርነታቸው የመልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ ዕረፍት አስደንጋጭ መሆኑን ገልጠው ከዚህ ቀደም ይደስባቸው የነበረውን መገፋትና በደል እርሳቸው ከመጡ በኋላ እንዳስቀሩላቸውና መልካም የሆነ አባታዊ ፍቅር እንደሰጧቸው ፣ምእመናንንም ከልባቸው ‹‹ልጄ›› የሚሉና ለአጥቢያቸው ምእመናንና ካህናት የሰላም መልእክተኛና ተምሳሌት ሆነው የተበተነውን ምእመን በፍቅር በመሰብሰብ የዕርቅ ማዕድ አቅራቢ አባት እና የልማት አርበኛ እንደነበሩ ገልጠዋል። እንደ ምእመናኑ ገለጻ መልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህ ለልማት፣ለሰላምና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከነበራቸው ከፍተኛ ጉጉትና ትጋት ጋር በሁሉም ዘንድ እጅግ በመንፈሳዊ አገልግሎት የሚወደዱ፣ የዘርና የገንዘብ ፍቅርን የናቁ፣ በምእመናን እምነትና ፍቅርን ያገኙ፣ የወንጌል አርበኛና የማኅሌቱ ቀንዲል ነበሩ ሲሉም ይገልጿቸዋል። በሁሉም የአገልግሎት ቦታ የሚገኙ፣ ሌሊት በማሕሌቱ አድረው ማለዳ ደግሞ በዐውደ ምሕረት ላይ ምእመናን የሚያስተምሩ፣ በአንድ ወገን የጸሎት በሌላ ወገን የሥራ እንዲሁም በአንድ ወገን የፍቅር በሌላ ወገን የሥርዓት ሰው እንደነበሩ ምስክርነታቸውን የሰጡት የደብሩ ካህናትና ምእመናን የመልአከ ፀሐይ ደሣለኝ ስሜነህን ዜና ዕረፍት ድንገት በመስማታቸው እጅግ በጣም እንዳዘኑና እንደደነገጡ ገልጠዋል። በመጨረሻም “በረከትዎም ከኛ ጋር እንደሆነ እናውቃለን። የደብራችንን ታሪክ ለልጆቻችን ስንጽፍ የእርስዎ ስም ሁል ጊዜም ከፊት ይሆናል። ልጆቻችን ‹‹ይህ ሐውልት የማን ነው›› ሲሉንም ደስ እያለን የምንተርከው ሥራዎ በልባችን ለዘለዓሙ ይኖራል” ብለዋል።

# የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩ ወጣቶች የትውልድንና የሀገርን ስብራት ይጠግናሉ

**ክፍል ሁለት**



ከግራ ወደ ቀኝ መምህር ጥበቡ ጌታቸውና አቶ ምትኬነህ ዓለማየሁ

ካሣሁን ለምለሙ

***የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረጽ ያነሣሣችሁ (መነሻው) ምንድን ነው? የአካታችነትና የአፈጻጸም ሂደቱስ ምን ይመስላል?**

**መምህር ምትኬነህ፡-** የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ እንደ መነሻ የወሰድነው በሰንበት ትምህርት ቤቶች ያለው የተዘበራረቀና ቅርፅ የሌለው የትምህርት አሰጣጥ ሂደትን ነው። አንዳንድ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሥርዓተ ትምህርት የተደገፈ ዓይነት ትምህርት ይሰጡ የነበሩ አሉ።ለአብነትም አራዳ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስና ምስካዬ ኀዙናን መድኃኔዓለም አብያተ ክርስቲያናት ከሌሎች ቀድመው የሰንበት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርትን ተለማምደዋል።እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በምሳሌነት ከመጠቀሳቸው በተጨማሪ በየሰንበት ትምህርት ቤቶች ለወጣቶች ይሰጡ የነበሩ ትምህርቶች በሥርዓተ ትምህርት የተደገፈ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በየአጥቢያዎች ባሉ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በኩል የነበረውን ዘልማዳዊ የትምህርት አሰጣጥ ልማድ መቀመርና ሥርዓት ማስያዝ በጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት አስፈላጊውን ሁሉ ሲያደርግ ቆይቷል። ከዚህ በተጨማሪም ለሥርዓተ ትምህርቱ ቀረፃ ሊያግዙ የሚችሉ የሀብት ግብአቶችን ማሰባሰብ ተችሏል። የዘመናዊው የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ትምህርት በተቀራረበ መንገድ እንዴት ሊሰጡ እንደሚችሉ በማሰብ ጭምር ሥርዓተ ትምህርቱን ለመቅረፅ ተሞክሯል። ሰንበት ትምህርቶች እንደ ዘመናዊው ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ስለሚያስፈልጋቸው ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ያገናዘበ ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ ስለአስፈለገ ሥርዓተ ትምህርቱን ለመቅረፅ ከ፳፻ ዓ.ም ጀምሮ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። በሥርዓተ ትምህርቱ ቀረፃ ወቅት በዘመናዊው የትምህርት ዘርፉ በመምህርነት ሙያ የተሠማሩ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል።

እነዚህ አካላት ሥርዓተ ትምህርቱ ከመቀረጹ በፊትም በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥልጠና በበጎ ፈቃድ ሲያገለግሉ የነበር ናቸው። በቤተ ክርስቲያን በሚሰጡት ትምህርቶች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ መቆየታቸው ለሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ እገዛ እንዲያደርጉ አግዟቸዋል። በሥልጠናና ትምህርት ዙሪያ ልምድ ያካበቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶችም ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል።ሥርዓተ ትምህርቱን ለመቅረፅ እነዚህ መምህራን መጀመሪያ ግብአት ሲሰበስቡ ቆይተዋል። ለሥርዓተ ትምህርቱ

ቀረጻ ግብዓት የሚሆኑ ጉዳዮች በሙሉ ተደራጅተው ሥራው ከተጀመረ በኂላ ረጅም ጊዜ ወስዷል፡፡ አብዛኛው የሥራው ተሳታፊዎች በትርፍ ጊዜያቸው የሚሠሩ በመሆናቸው ሥራው ስምንት ዓመታት ያህል ወስዷል፡፡ጊዜው ወስዶ በተረጋጋ መንገድ መሥራቱ የበሰለና አካታች ሥርዓተ ትምህርት እንዲሆን አግዟል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጥ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት መመራታቸው የነገ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ የሆነው ወጣት የአብነት ትምህርትን በረከትና ጸጋ ሳያገኝ እንዳያልፍ ለማድረግ ያግዛል፡፡የአብነት ትምህርት ምንነትን ያላወቀና እርሾው የሌለው ቤተ ክርስቲያንን ሊረከብ እንደማይችል በማመን በትንሹ የአብነት ትምህርትን በሥርዓተ ትምህርቱ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡የአብነት ትምህርትን ተምረው የማለፉ ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች ዕድል የሚሰጥ ሆኖ ሥርዓተ ትምህርቱ ተዘጋጅቷል፡፡

በሥርዓተ ትምህርቱ ቀረጻ ወቅት አብዛኛዎቹ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ በየአጥቢያውና በየማደራጃ መምሪያው ያሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ቅርፅ በዝግጅትና በግምገማው እንዲሳተፉ ተደርጓል፤ ከዚህ በተጨማሪም የነገረ መለኮት (የቴዎሎጂ) መምህራንን ለማሳተፍ ተሞክሯል፤ በአጠቃላይ ልምዱና ዕውቀቱ ያላቸው መምህራንና ሊቃውንት በዝግጅቱ በተለያየ መንገድ ተሳትፈውበታል፡፡ ያም ሆኖ ግን ሥርዓተ ትምህርቱ የተለዩ ክፍተቶችና ጉድለቶች እንዳሉበት በሁላችንም የሚታመን ነው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ክፍተቶችን ለማስተካከልና ለማሻሻል ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሥርዓተ ትምህርቱ ሲቀረጽ በተቻለ መጠን በባለሙያዎች ተገምግሞ የተሰጡት አስተያየቶችና ጥቆማዎች ጭምር በሰነዱ እንዲካተት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘት በተመለከተ ይዘቶቹ በተለያዩ ደረጃዎች የተከፈሉ ሲሆን በደረጃ አንድ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት እስከ ዐሥር ያሉ ሕፃናት፣ በደረጃ ሁለት ላይ የተቀመጡት ደግሞ ከአሥራ አንድ እስከ አሥራ አራት የዕድሜ በደረጃ ያሉት ናቸው፤ ደረጃ ሦስት የተቀመጡትም እንዲሁ ከዐሥራ አምስት እስከ አሥራ ስድስት ዕድሜ ያላቸው ሲሆኑ ሲሆን በደረጃ አራት ላይ የተቀመጡ ደግሞ በዕድሜያቸው ከዐሥራ ስምንት ዓመት በላይ የሆኑት የሚያካትት ነው፡፡ ዘመናዊ ትምህርት ደረጃ ሲታይ ደግሞ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ወጣቶችን ሥርዓተ ትምህርቱ ያካትታል፡፡ እነዚህ ወጣቶችን ያካተተው ሥርዓተ ትምህርትም በቀጣይ ሙሉ መማሪያ መጽሐፍ የሚዘጋጅለት ይሆናል፡፡

ስለሆነም እስካሁን ድረስ የአንደኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አጠናቀን ለሁሉም አህጉረ ስብከት አሠራጭተናል፡፡ የተላከው መጽሐፍት ብቻ ሳይሆን ሥርዓተ ትምህርቱ ጭምር ነው፡፡አሁን ሁሉም አህጉረ ስብከት አንደኛ ክፍል ላይ በትግበራ ላይ ናቸው፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱ የራሱ የሆነ ትግበራና ክትትል ሂደት አለው፡፡ ይህንንም የሚገመግምና የሚከታተል ክፍል አለ፤ መጻሕፍት ዝግጅት ክፍል የሚባል አለ፣ ትግበራ ክፍል የሚባልም አለ፡፡ ሌሎችም ተጨማሪ ክፍሎች አሉ፡፡ በሂደቱ ውስጥ ሌሎች ክፍሎችም የሚሳተፉበት ሁኔታ አለ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሥርዓተ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ የሁለተኛና የሦስተኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡

አፈጻጸሙን በተመለከተ ከሕፃናት እስከ ጎልማሳ ድረስ በሥርዓተ ትምህርቱ ማዕቀፍ የመማር ዕድል አለው፡፡ የትምህርት ሥርዓቱ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ብቻ ተሰጥቶ የሚቆም አይሆንም፡፡ ይልቁንም በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እንዲሰጥ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህንን ለማድረግ የበጀትና ተያያዥ ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ አፈጻጸም ደግሞ ከአጥቢያ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን አካል ጀምሮ የበጀት ፈሰስ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰንበት ተማሪዎች ስለ በጀት ሳያስቡ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ይታሰባል፡፡

ከዚህ ቀደም ከላይ እስከ ታች ያለው አካል የበጀት ምንጭ ሆኖ በሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ ሂደት ላይ አገልግሏል፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱ ያላካተተው ቢኖር የልህቀት ማእከል ነው፡፡ ይህንን የልህቀት ማእከል ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች ይጀመራሉ፡፡ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል በሰንበት ትምህርት ቤት ያለፉ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስቀጠል የልህቀት ማእከሉ ያግዛል፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዐሥራ ሁለተኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኂላ ወደ ልህቀት ማእከሉ በመግባት የተሻለ ዕውቀትና ልምድ እንዲያካብቱ ይደረጋል፡፡ይህ ማለት ተማሪዎች ወደ አብነት ትምህርት ቤት፣ ወይም ወደ ነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ሄደው እንዲማሩ ይደረጋል ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የልህቀት ማዕከሉ በአብነትና በነገረ መለኮት ትምህርቶች እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከፍተኛ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንደ ልህቀት ማእከልነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ይህ የልህቀት ማእከል ታዲያ ከዐሥራ ሁለተኛ ክፍል በታች ያሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ይሆናል፡፡ ሌሎች የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶችም ይህንን ተግባር እያሰፉና እያዳበሩ የሚሄዱበት አሠራር ይመቻቻል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡-ሥርዓተ ትምህርቱ የሚመልሳቸው ቁልፍ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሥርዓተ ትምህርቱ ተደራሽነትስ እንዴት ይገለጻል?**

**መ/ር ጥበቡ፡-** ሥርዓተ ትምህርቱ በዋናነት የተለያዩ ቁልፍ ጥያቄዎችን የሚመልስ ሲሆን እነዚህም የመጀመሪያው የይዘት ጉዳይ ነው፤ ይህም ምን እንደሚማሩ የሚያብራራ ነው፡፡ ሁለተኛውም ለምንድነው የሚማሩት? የሚለውን ዓላማ የሚመልስ ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ እንዴት ማስተማር እንዳለብን (ዘዴውን) የሚመልስ ሲሆን አራተኛውም እንደዚሁ የተማሪውን ልምድና ተሞክሮ ግምት ውስጥ አስገብቶ አስተማሪው በምን መልኩ ያስተምር የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፡፡ አስተማሪው

ለማስተማር እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት፣ ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን እንዲሁም የዋቢ መጻሕፍት አጠቃቀምን ጭምር ያስቀምጣል። የመማሪያ ክፍል ሁኔታና የተማሪዎችን የዕድሜ ክልልም ሥርዓተ ትምህርቱ ይወስናል። ሥርዓተ ትምህርቱ የራሱ ግብ ሲኖረው ይኸውም ትውልድን ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ማትረፍ ነው። ይህንን ለማድረግ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያው ተግባራቸው ትምህርት መሆን ያለበት። እንደ ሀገርና እንደ ቤተ ክርስቲያን አሁን የደረስንበት ስብራትና ውድቀት ምክንያቱ ትምህርት ነው። በትምህርት ክፍተት ምክንያት የደረሰብን ውድቀትና ስብራት ሊታረም የሚገባው በትምህርት በመሆኑ በተደራጀና ተከታታይነት ባለው ሥርዓተ ትምህርት ሰንበት ትምህርት ቤቶችን መምራት ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩ ወጣቶች የትውልድንና የሀገርን ስብራት ሊጠገኑ ይችላሉ። ወጣቶች ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ያለማምጣትና የተደራሽነት ችግር በየአጥቢያው ማየት የተለመደ እየሆነ በመምጣቱ ይህንን ለመቅረፍ ሥርዓተ ትምህርቱ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ይሆናል። ወጣቶች ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት መጥተው እንዴት መማር እንዳለባቸው ያስገነዝባል። ለዚህ አጋዥ የሚሆነው ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱም ሆነ የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት በብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ የተቃኘ ሊሆን እንደሚገባ እናምናለን። ይህንን ለማድረግና ሰነዶቹን በሀገራችንና በውጭ ሀገር ቋንቋዎች ጭምር ለመተርጎም የተጠናከሩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ከቋንቋ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት በየክፍሉ ወይም በአካባቢ ማስተባበሪያዎች ለማቋቋም ዕቅድ ተይዞ ወደ ተግባር ተገብቷል። በዚህ ወቅት የአንደኛ ክፍል የትምህርት አሰጣጥ ሂደትን ለማገባደድ ጫፍ ላይ ደርሰናል። ከዚህ በተሻለና ፈጣን በሆነ መንገድ ተደራሽ ለመሆን ደግሞ መካነ ድርን በመጠቀም ውጭ ሀገር ያሉ ወንድሞችና እኅቶች የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ይሆናል። ለዚህም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በተለይ ቀጥታ መካነ ድርን (e-learning) በመጠቀም የሚከወን ይሆናል። ይህ በአይሲቲ ክፍሉ አስተባባሪነት የሚሠራ ይሆናል። እነዚህ ተግባራት ጅምር ቢሆኑም ክትትልና ድጋፍ ይፈልጋሉ። በቋንቋዎች ላይ ከፍተኛ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል። በዚህም የተነሣ የሰንበት ትምርት ቤት ማደራጃ መምሪያው አስቦ አቅዶ በጀት ይዞ ለመሥራት እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ከሥርዓተ ትምህርቱ ትግበራ በኋላ በሂደት እየታየ ማሻሻያ የሚደረግበት ሲሆን አሁን ችግሩን ለማየት ደግሞ በሁሉም ደረጃ ተግባራዊነቱ ይቀጥላል።

**ስምዐ ጽድ፡- ሥርዓተ ትምህርቱ በቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ላይ ምን ለውጥ ያመጣል ተብሎ ይታሰባል?**

**አቶ ምትኬነህ፡-** ከሰንበት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት አኳያ ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶቿን የምታስተምርበት ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት አልነበራትም። አሁን የተቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት ግን በቤተ ክርስቲያኗ ዘንድ ከሰንበት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ አንጻር ሲታይ ይህ የመጀመሪያው ነው።ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ የትምህርት ሥርዓት ቢኖራትም ወጥና ተከታታይ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ግን አልነበራትም። ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት መኖሩ ትምህርቶች ወጥና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲሰጡ ያግዛታል። ይህ ተግባር የቤተ ክርስቲያንን የትምህርት ዘርፍ ሁለንተናዊ እድገትና መሻሻል እንዲያመጣ እንዲሁም የተደራሽነትና የተሳታፊነት ምጣኔ እንዲጨምር ያደርጋል። ስለሆነም ሥርዓተ ትምህርቱ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዘርፍ ላይ ፈጣን የሆነ ለውጥ ያመጣል። ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የራቀውን ትውልድ ለመሰብሰብም ያግዛል።

**ጽምዐ ጽድቅ፡-ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**መምህር ጥበቡ፡-**ሰንበት ትምህርት ቤት የተቋቋመው የቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና አውቀው የሚያሳውቁ ወጣቶችን ለማፍራት ነው። የቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና ጠንክሮ ማስተማር ደግሞ አስፈላጊ በመሆኑ የተደራጀ ትምህርት ለማስተማር የግድ ሥርዓተ ትምህር መቅረጽ አስፈልጓል። በግሎባላይዜሽን ተፅዕኖ የተወሰደውን ወጣት በተግባርና በሥርዓተ ትምህርት የተደገፈ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። በሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑ ሃይማኖትና ስብዕና ያላቸውን ወጣቶች ማፍራት ነገ ላይ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን የሚረከብ ትውልድ ለመቅረፅ ያግዛል። ወጣቶች ወደ እውነተኛው ሕይወት እንዲመጡና ሕይወታቸውን በንስሓ የተቃኘ እንዲሆን ማስተማር ያስፈልጋል። የሥርዓተ ትምህርቱ ስኬት የሚለካውም በቤተ ክርስቲያን ሱታፌ የጸኑ ወጣቶችን ማፍራት ሲቻል ነው። የሚያስቀድስ፣ በማኅሌቱ የሚሳተፍ፣ ቤተ ክርስቲያንን በሁሉ ዘርፍ የሚረዳና መንፈሳዊ ሕይወትን በተግባር የሚኖር ወጣት ማፍራት የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማ ነው።

**ስምዐ ጽድቅ፡-ለነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ይስጥልን**

**የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች፡-** እኛም ለዚህ ቃለ መጠቅ ስለጋበዛችሁን እናመሰግናለን!!!

# በዓታ ለማርያም ለልጆች

ምኒልክ ብርሃኑ

እግዚአብሔር የሚወዳችሁ፣ እናንተም የምትወዱት ልጆች እንደምን ሰነበታችሁ? የአምላካችን የልዑል እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን:: እንኳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ ለገባችበት በዓል በሰላም አደረሳችሁ:: ልጆች! ይህ በዓል በዓታ ለማርያም ይባላል:: የሚከበረው ደግሞ ታኅሣሥ ሦስት ቀን ነው:: በዛሬ ቆይታችን ታኅሣሥ ሦስት ቀን ስለሚከበረው እና እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ ስለገባችበት ታሪክ እንማራለን ማለት ነው::

ልጆች! በዓታ ለማርያም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ፴፫ (ሠላሳ ሦስት) በዓላት መካከል አንዱ ሲሆን የሚከበረውም ደግሞ ታኅሣሥ ሦስት



እመቤታችን ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ እንደገባች

ቀን ነው::በዓታ ለማርያም ቃሉ የግእዝ ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበትን ዕለት ታሳቢ በማድረግ የሚከበር በዓል ነው::

ልጆች! የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እናቷ ቅድስት ሐና፣ አባቷ ደግሞ ቅዱስ ኢያቄም ይባላሉ:: ሐና እና ኢያቄም ቀድሞ ልጅ ስላልነበራቸው እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ሁልጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ እየሔዱ ይጸልዩ ነበር:: በጸሎታቸውም “ወንድ ከሆነ ካህን ሆኖ ቤተ መቅደስ እንዲያገለግል፤ ሴት ከሆነች ደግሞ ውኃ ቀድታ ፈትል ፈትላ ቤተ እግዚአብሔርን እንድታገለግል ላንተ እንሰጣለን” ብለው ስለት ተሳሉ::

ታዲያ ልጆች! ከብዙ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ስእለታቸውን ሰምቷቸው ሐና ፀነሰች:: ከዚያም እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግንቦት አንድ ቀን ተወለደች:: ሐና እና ኢያቄም እመቤታችን ድንግል ማርያምን እግዚአብሔር ስለሰጣቸው እጅግ በጣም ደስ አላቸው:: በፍቅርም እየተንከባከቡ እስከ ሦስት ዓመት አሳደጓት::

ከዚያም ሦስት ዓመት ሲሆናት በስዕለታቸው መሠረት ለቤተ ክርስቲያን ወስደን እንስጣት ተባባሉ:: በኋላ ታኅሣሥ ሦስት ቀን በጠዋቱ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘዋት ሄዱ:: በዚህ ጊዜ የቤተ መቅደሱ አገልጋይ ዘካርያስ ይባል ነበር::

ልጆች! ካህኑ ዘካርያስን ታውቁታላችሁ አይደል? አዎ! ዘካርያስ የቅድስት ኤልሳቤጥ ባለቤት፣ የመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ አባት ነው:: ሥራው ቤተ መቅደስን ማገልገል ነበር:: ከዚያም ሐና እና ኢያቄም ወደ ዘካርያስ ቀርበው “በስእለታችን መሠረት ይኸው ልጃችንን ማርያም ይዘን መጥተናል” አሉትና አስረከቡት::

እርሱም “ቃላችሁን ማክበራችሁ ጥሩ ነው፤ ነገር ግን የምግቧ ነገር እንዴት ይሆንልናል፤ ገና ሕፃን ልጅ ናት ምንድን ነው የምንመግባት?” አላቸው:: ድንግል ማርያም ገና ሕፃን በመሆኗ ዘካርያስ የሚያበላት ነገር ጨነቀው::

በጣም ሲጨንቀው ጊዜ ሕዝቡን ሊያማክር ደወሉን ደወለ፤ ሕዝቡም ደወሉን ሰምተው ተሰበሰቡ።

ማርያምን ምን እንደሚመግባት መነጋገር ጀመሩ። ነገር ግን ሁሉም ምንም መፍትሔ ሊያገኙ አልቻሉም። በኋላም ስለእመቤታችን ምግብ ሲያወጡ ሲያወርዱ እየተጨነቁ ሳለ አንድ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ተከሠተ።

ካህናቱና ሕዝቡ ተሰብስበው ሳለ በመካከላቸው መልአኩ ፋኑኤል ከሰማይ ወረደና በመካከላቸው ተገኘ። እነርሱም እጅግ ተገረሙ። ዘካርያስም መልአኩን ባየው ጊዜ ተደነቀ። መልአኩ ፋኑኤልም ኅብስተ ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዞ ነበር።

በዚህ ጊዜ ዘካርያስ ለርሱ የመጣ መስሎት ሊቀበለው በተነሣ ጊዜ ወደ ላይ ራቀበት።ሌሎች ካህናትም እየተነሡ መልአኩ የያዘውን ሊቀበሉት በተነሡ ጊዜ ወደ ላይ እየወጣ ይሸሻቸው ጀመር። እንደገናም ለሐና እና ኢያቄም ነው የመጣው ብለው እንዲቀርቡ አደረጓቸው፤ ለእነርሱም ራቀባቸው።

በመጨረሻም ዘካርያስ "የእግዚአብሔር ሥራ አይታወቅም፤ ሁል ጊዜ ድንቅ ነው፤ ስለዚህ ምን አልባት መልአኩ የመጣው ለዚች ሕፃን ይሆናልና ይዘሻት ቀረብ በይ" አላት። ሐናም ሕፃኗን ማርያምን



መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤል ማርያምን ሲመግባት

ይዛ ወደ መልአኩ አቀረበቻት። መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤልም ወደ ቅድስት ማርያም ተጠጋና ወደ ላይ

ከፍ አደረጋት። ከዚያም ም አንዱን ክንፉን አንጥፎ፤

በአንድ ክንፉ ደግሞ ጋርዶ ከሰማይ ያመጣውን ኅብስተ ሕይወት እና ጽዋዕ ሕይወት መገባት።ከዚህ

በኋላ ከፍ ካደረጋት ቦታ መልሶ አስቀመጣት፤ ከዚያም

ወደ ሰማይ ዐረገ።

በዚህ ጊዜ የነበሩት ሁሉም ባዩት ነገር በጣም ተደነቁ። ይህን ጊዜ ካህኑ ዘካርያስና ሕዝቡም ሲያስጨንቃቸው የነበረው የምግቧ ነገር ስለነበር እግዚአብሔር

እንደሚመግባት ተረዱ። በቤተ መቅደስ እንድትኖርም አስገቧት፤ ይህም ቀን ታኅሣሥ ሦስት ቀን ነበር።እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ሰማያዊ ኅብስትና ሰማያዊ መጠጥ እየተመገበች ፲፪ ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች።

ልጆች! ታሪኩን በጥሞና ተከታተላችሁ አይደል? ጎበዞች! ታኅሣሥ ሦስት የልዑል እግዚአብሔር እውነተኛ መቅደስ የምትሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበትን ዕለት የምናስብበት እንደሆነም ተረድታችኋል ማለት ነው። ከታሪኩም ከቤተ ክርስቲያን መራቅ እንደሌለባችሁ፤ ልጆች ደግሞ ስለምትበሉት እና ስለምትጠጡት ነገር መጨነቅ እንደሌለባችሁ፤ የሚመግባችሁና የሚጠብቃችሁ እግዚአብሔር እንደሆነ፤ እንዲሁም አምላካችን ከብዙ ነገር እንደሚጠብቀን ከዚህ ታሪክ እንማራን።

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን። የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። በሚቀጥለው ጊዜ በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ድረስ ደኅና ሁኑ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

# የጎዳና ላይ ልመና

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረው ክርስቲያኖች በሚሰጡት ዐሥራት በኵራት፣ መባእና በተለያየ የልማት ውጤቶች በምታሰባስበው ገንዘብ ነው:: ክርስቲያኖችም ዐሥራት በኵራት የመስጠት ግዴታ አለባቸው:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚቋቋመው፣ ቤተ ክርስቲያንም የሚያስፈልጋትን አሟልታ አገልግሎቷን የምታቀላጥፈው በሚተጉ ምእመናን ፈቃድና ግዴታ ነው::

በቀድሞ ዘመን የቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች ከፍተኛ የሀብትና ሥልጣን ባለቤት በነበሩ ክርስቲያን መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ነገሥታትና ልዑላን ድጋፍ ነበረ:: እነዚህ ወገኖች ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገውን ሁሉ በማቅረብ አገልግሎቱ እንዲስፋፋ እና እንዲዳብር ያደርጉ ነበር:: በመሆኑም የእነዚህ ደጋፊዎች በሀገሩ ፖለቲካ ምክንያት ሚናቸው ሲጠፋ፣ ሀብት ንብረታቸውንም ሲያጡ የሚደግፏቸው አጥቢያዎችም ለአገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ በዚያው መጠን እየቀነሰ መጣ::

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተሳታፊም ተጠቃሚም መላው ሕዝበ ክርስቲያን ስለሆነ ባላቸው አቅም የሚጠበቅባቸውን እያደረጉ አገልግሎቱን ለማስቀጠል ርብርብ አድርገዋል:: ይህም እንደ እነ አቡነ ቴዎፍሎስ በመሰሉ ብልህ አባቶች አርቆ አሳቢነትና አመራር የሰበካ ጉባኤ አደረጃጀት ተፈጥሮ፣ ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገውን እንዲያቀርቡ፣ በማስተማርና በማሳመን ለካህናት ደመወዝ፣ ለንዋየ ቅድሳት፣ ለሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ወዘተ. አገልግሎት በምእመናን ትከሻ የሚሸፍን ሆኗል::ከዚህ ባለፈም በስእለት፣ በስጦታ የሚገቡ ገቢዎችም ተጨማሪ አቅም ሆነዋል::

ይህንን አሠራርም በሕግ ለመምራት በቃለ አዋዲ አስፈላጊ የሕግ መመሪያ ይዘቶች ሁሉ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ውለዋል:: በዚህ መንገድ ጠቢባን የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ትጉሃን ምእመናን የነበረውን የፖለቲካ ሥርዐት ለውጥ ያመጣውን ቀውስ በጥበብ ተሻግረው፤ የሶሻሊስት ኮሚዩኒስት የፖለቲካ ርእዮትም የፈጠረውን ወጥመድ ተቋቊመው፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚባለው የፖለቲካ ሤራና የመናፍቃን ቅሰጣ ሁሉ ሳይበግራቸው የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እስከ አሁን አስቀጥለዋል::

ይህ ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት፣ በሕግና መመሪያ እያስተዳደሩ የሚያስፈልጋትን የገንዘብ፣ የንዋየ ቅድሳት እና ሌሎችንም ቁሳ ቁሶች በማሟላት የሚሠራበት አካሔድ ግን ፈተና አልገጠመውም ማለት አይደለም:: ከእነዚህ ፈታኝ ሁኔታዎች አንዱ ቤተ ክርስቲያን የገጠማትን ፈተና መነሻ ያደረገ፣ በካህናት እና በአጥቢያዎች ስም በጎዳና ላይ የሚደረግ ልመና መስፋፋቱ ነው::

የጎዳና ላይ ልመና እጅግ አደገኛ የቤተ ክርስቲያን ፈተና ነው:: ይህ የሚባልበትም መሠረታዊ ምክንያቶች አሉት::

1ኛ/ በጐ ገጽታን ማጥፋት:- ቤተ ክርስቲያን የምትታወቅበት መልክ ልመና ሳይሆን የትጉሃን፣ የባለሙያዎች፣ የጠቢባን ክርስቲያኖች ቤት መሆኗ ነው:: ክርስቲያኖችም የቤተ ክርስቲያን ናቸው::ቤተ ክርስቲያን ማለትም ምእመናን ናቸው:: ክርስቲያኖች በቤታቸው ተገኝተው የሚገባውን የሚያደርጉበት ሥርዓት አለ፤ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ወጪዎችንም በአጥቢያ ዐውደ ምሕረት ላይ በይፋ የምትጠየቅበት አሠራር አለ፤ ስለዚህ ለልመና ወደ ጎዳና ላይ የሚያስወጣ ምክንያት ትርፉ ልጆች የሌሏት፣ ደጋፊ ያጣች፣ በቅጽሯ የሚገኝ አማኝ ያጣች ስለሚያስመስል በየጎዳናው ላይ ልመና መስፋፋቱ በጐ ገጽታዋን የሚያጠለሽ ሆኗል::

2ኛ/ የግለሰቦች መጠቀሚያ መሆኑ:- በቤተ ክርስቲያን ስም በግል የሚደረግ የልመና ገንዘብ ለአጥቢያዎች በትክክል ስለመድረሱ ምእመናንን ያጠራጥራል:: አንድ ሰው ወይም ሁለት ሰዎች ተሸፋፍነው በዐደባባይ ቃጭል እያቃጨሉ፤ በማይክሮፎን እያጮሁ፤ ሙስሊሙም መናፍቁም፣ ከሃዲውም በሚረማመዱበት ሁሉ ለዛ በሌለው ልመና የገንዘብ ያለህ ሲሉ ነገሩ ለግል መጠቀሚያ ላለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ አንዳችም ነገር የለም:: ማስረጃ የሚመስል የሆነ ነገር ይዞ መለመንም ለቤተ ክርስቲያን ጎጂ መሆኑ

እንዳለ ሆኖ፤ ለዚያ የሚሆን ነገር ሳይዙ የሚታዩት ደግሞ ብዙዎች ናቸው::ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ስም ለግለሰቦች ጥቅም ማግበስበሻ እየሆነ ነው::

ሌላው በጎዳና ልመና ላይ የሚታዩ የተወሰኑትም የታሸገ የሚመስል ሙዳየ ምጽዋት እንኳን የሌላቸው ናቸው:: ነጠላ ከሥዕል አጠገብ ተነጥፎ ተጠያቂነትን በማሳይ የሚሰበሰብ ገንዘብ መቼ፣ ስንት፣ ከእነማን እንደተሰበሰበ ለመቆጣጠር እንኳን በማያስችል መንገድ የሚሠራ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል::

3ኛ/ ንዋያተ ቅድሳት ክብር እያጡ መሆኑ:- በልመና ጊዜ የሚለምኑ ሰዎች በየጎዳናው የሚይዟቸው ሥዕላት፣ ጃንጥላ፣ ቃጭል፣ ልብሰ ተክህኖ ወዘተ. አድፈው፣ ደብዝዘው፣ ተቀዳደው፣ ዐደባባይ መሬት ላይ ለልመና ተነጥፈው ሲታዩ እንዴት ክብር እያጡ እንደሆነ በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል:: ለቅዳሴ፣ ለውዳሴ የሚያገለግሉ ቃጭሎች በየጎዳናው አላግባብ ሲቃጨሉ ማየት እየተለመደ መጥቷል:: ለአገልግሎት በሥርዐት መለበስ ያለበት ልብሰ ተክህኖ አድፎ ተቀዳዶ በየዐደባባዩ የካህናትን ገጽታ ሲያጠለሽ ይውላል:: ካህናት እንደ ለማኞች፣ እንደ ችግረኞች እየታዩ በየትውልዱ አእምሮ በጥያቄ ውስጥ እንዲኖሩ እየተደረገ ነው::መስቀሉም በሚገባቸው ሰዎች ስለመያዙም እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: ከዚያም አልፎ ሴቶችም ተሰባስበው፣ ሥዕል ይዘው፣ ነጠላ አደግድገው ስለሚታዩ ወዴት እየሄድን ነው? ያስብላል::

4ኛ/ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጡ ማባረሪያ መሆኑ:- በርካታ ምእመናን ለመሳለም ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን መባእ፣ ዐሥራት በኵራት ለመስጠት ወደ የአጥቢያቸው ያመራሉ፤ ስእለታቸውንም ያስገባሉ:: ይሁን እንጂ የጎዳና ላይ ልመና የፈጠረው ዕንቅፋት:- ምእመናን በገርነት ምጽዋታቸውን፣ ስእለታቸውን፣ ዐሥራታቸውን ወዘተ. በአጥቢያ ተገኝተው እንዳይሰጡ፤ ለጸሎትና፣ ለምስጋና የሚኖራቸውን የትጋት፣ የፍቅር ዝንባሌ እንዳይጨምር፣ የዕጣኑ ሽታ፣ የደወሉ ጥሪ፣ የካህኑ ቡራኬ እንዳይደርሳቸው ያደርጋል::

ቃለ እግዚአብሔር ሰምተው፣ ከአጋንንት ወጥመድ እና እስራት ለመፈታት  የሚመጡበትን ትጋትና ፍላጎት የሚሰልብ፣ የአስመሳይ ካህናት የልመናን መንገድ የሚከፍት ሁኖላቸዋል:: አንዳንዶችም ቤተ ክርስቲያንን እዚያ ያገኙ እስኪመስላቸው ድረስ ገንዘባቸውን ሰጥተው፣ በልመና አድራጊው ሰው መስቀል ተሳልመው፣ በሥዕሉም ፊት ጸልየው መሄዳቸው ሌላው አደገኛ ፈተና ነው::

ስለዚህ ይህ የቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚያሳጣ ነገር በጊዜ መቆጣጠር ካልተቻለ ፈተናዋ የበዛ ይሆናል:: ይህንን ለማስተካከል ልዩ ልዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ መፍጠን አለመቻሉም ትዝብት ላይ እየጣለ ነው::

የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርም ከአጥቢያ ውጪ በሌሎች የሕዝብ ጎዳናዎች የሚደረጉ ልመናዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉ አለመሆናቸው በየሚዲያዎቹና በየአጋጣሚዎቹ ሁሉ ይፋ ማድረግ አለበት:: በየደረጃው ላለው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በዚህ ረገድ እርምት እንዲወስድ መመሪያ ማስተላለፍ ያስፈልጋል::

ከምንም በላይ ግን ሁነኛው መፍትሔ ምእመናንን ማስተማርና ማስገንዘብ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ስም በሚደረጉ ልመናዎች እየደረሰ ያለውን የገጽታ መበላሸት፣ የምዝበራ፣ የንዋየ ቅድሳት ውርደት ሁሉ ለምእመናን ማስገንዘብ ያስፈልጋል:: ለለማኞች በተባበርን ቁጥር እነዚህን ጥፋቶች እንዲፈጸሙ እየገፋፋን መሆኑን መንገር ያስፈልጋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ምእመናን ገንዘባቸውን፣ ስእለታቸውንና ዐሥራት በኵራታቸውን በጎዳና ላይ በመስጠታቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን መድረስ ባለመቻሉ የሚፈጥረውን የአገልግሎት መዳከም ማስገንዘብ ያስፈልጋል:: ምእመናን በዚህ ረገድ ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎቷ ተሳታፊ ባለቤትም ተጠቃሚም እነሱ መሆናቸውንና እንደ ቤተሰብ በቅርበት እንጂ እንደ ባዕድ በሩቅ የሚያደርጉት ግንኙነት አግባብ አለመሆኑን ማስረዳት ይጠበቅብናል::

የጎዳና ላይ ሥዕልና መስቀል ይዞ ልመና፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናን፣ በአጠቃላይ በሀገር ሕግና ሥርዓት ውስጥ ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖ በአስቸኳይ መቅረፍ አለመቻል ሁሉም ወገን በትትዝብት እንዲያየው የሚጋብዝ መሆኑን እንወቅ እንላለን::

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር::***

# ካልተበቀልኩ ዕረፍት የማገኝ አይመስለኝም

**ክፍል ሁለት**

***የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

እኛ በየሰዓቱና በየደቂቃው ለበቀል በሚያነሣሣ ኃጢአት ሥራ ውስጥ ስንዋኝ እየዋልን እያደርን ሳለ እግዚአብሔር ግን ዳካሞች ናቸው ልሸከማቸው ብሎ በታላቅ ትዕግሥትና ቸርነቱ በያዘን መንገድ እኛ ደግሞ አልፎ አልፎ አካልና ስሜታችንን የሚጎዱ ሰዎችን በትዕግስትና ከበቀል በመራቅ ለመሸከም እንድንጥር ተመክረናል፡፡ ይህንን ማድረግም ራሱን ጌታችንን መምሰል በመሆኑ የእርሱ ልጆች ለመባል የተገባን እንደሚያደርገን በቅዱስ ቃሉ ‹‹በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት፡፡ እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡›› (ማር ፲፩፥ ፳፭-፳፮) ተብለን ታዘናል፡፡

ስለዚህ እርስዎም ጠያቂያችን እግዚአብሔር ለእርስዎ በየዕለቱ የሚያደርገውን ትዕግሥትና የቸርነት ሥራ በማሰብ ከበቀል ለመራቅ አቅም እንዲያገኙ እንመክራለን፡፡ ይህ ማለት በእኅትዎ የደረሰ ጉዳት የእግዚአብሔር ዓይኖች የሚያዩት አጥፊውም በንስሓ ካልተመለሰ የእግዚአብሔር የበቀል ቁጣ የሚያርፍበት መሆኑን አይጠራጠሩ፡፡ የእኅትዎ ቁስል፣ ዕንባና የስሜት ስብራት ከፈጣሪዎ ዓይን የተሰወረ አይደለም፡፡በቀልም የእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሚሠሩ ግፎች ሁሉ መልስ አለው፡፡

እግዚአብሔር የምስኪኑን የናቡቴን ደም እንዴት እንደተበቀለ ማስታወስ ይገባል (፪ኛ ነገሥ. ፱፥፴–፴፯)፡፡ ናቡቴ የአባቶቹን ርስት ሊነጥቁት በሐሰት ክስ ደሙን አፍሰው የገደሉትን ንጉሥ አክአብና ክፉ ሚስቱን ሳይበቀላቸው አልቀረም፤ እጅግ በሚያስከፋ ሞት ሁለቱም እንዲቀጡ በማድረግ ለሰዎች መቀጣጫ እንዳደረጋቸው ማስተዋል ይገባል፡፡ እግዚአብሔር የንጹሑን የአቤልን ደም ያፈሰሰውን የገደለውን የወንድሙን የቃየል ክፋት እንዲሁ አልተወም፤ ቃየል በምድር ላይ ተቅበዝባዥና ተንከራታች ሆኖ እንዲሞት እንዴት እንደፈረደበት እናስተውል (ዘፍ ፬፥፩–፲፫)፡፡የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት የቀረጠውን ሄሮድስን እግዚአብሔር በትል ተበልቶ እንዲሞት እንደፈረደበት እናስተውል (ገድለ ዮሐንስ መጽምቅ)፡፡

እግዚአብሔር የብዙ ንጹሐንን እንባ አብሷል፤ የብዙዎችን ደም መልሷል፡፡በንስሓ የተመለሱትንም በቸርነትና በይቅርታው ጎብኝቷል፡፡ለተጎዱትም መጽናናትን ዕረፍትና ደስታን ሰጥቷል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ፡፡ ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡ ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና፡፡ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ፡፡›› (ሮሜ ፲፪፥ ፲፯-፳፩) በማለት በተናገረው ግሩም ቃል ሊጽናኑም ይገባል፡፡

የመንፈስ ስብራት የደረሰባት እኅትዎን እርስዎም ሆኑ ቤተሰብዎ ከአጠገብዋ ባለመራቅ፣ በማጽናናት፣ በመምከር እና በማበረታታት ከገባችበት የአካልና የሕሊና ስብራት እንድትላቀቅ በብርቱ መትጋት ይኖርባችኋል፡፡ በእምነቷ እንድትበረታ ቤተ ክርስቲያንን እንድታዘወትር፣ መጽሐፍ ቅዱስ እና የተለያዩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን እንድታነብ፣ ከመንፈሳዊ ወንድሞች እና እህቶች ጋር ጊዜዋን እንድታሳልፍ በማድረግ እንድትጽናና ብሎም ወደ ቀደመ ደስታዋ እንድትመለስ የበኩልዎን ድርሻ መወጣት ይገባል፡፡ እርስዎ እንደሚሉት ለበቀል መነሳሳት እና የበቀል ድርጊት መፈጸም እርስዎን ከወንጀለኛነት እና ከኃጢያተኛነት አያድንዎትም እርስዋንም ቢሆን ከደረሰባት ቁስል አይፈውሳትም፡፡

ግዚአብሔር ተበዳይ የሚክስበት፣ በዳይን የሚበቀልበት የራሱ ምስጢር አለው፡፡ የራሱም ኃይል አለው፡፡ ከእርሱም የሚበልጥ ባለሥልጣን፣ ኃያልና፣ እውነተኛ ዳኛ የለም፡፡ የሚገባንን ሽልማት የሚያስቀር፣ የሚገባንንም ቅጣት ያለምክንያት የሚተው አይደለም፡፡

እግዚአብሔር በጎን ለሚሠሩ ከአስመሳዮች ለይቶ በረከቱን ረድኤቱን ክብሩን ጸጋውን እንደሚሰጠው ሁሉ በሰው ላይ ክፉ ያደረጉ፣ ንጹሐንን የበደሉ ሰዎችን የሚበቀልበት ወይም ይቅር የሚልበት የራሱ ምስጢር አለው፡፡ ስለዚህም ሰዎች ሲያጠፉ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ እንዲበቀሏቸው ሳሆን ራሱ ባለቤቱ ፈጣሪያቸው እንዲበቀላቸው፣ እንዲቀጣቸው ፈቃዱን በትእዛዙ አሳይቷል፡፡

ፈጣሪ ግፈኞችን መበቀል ብቻ ሳይሆን ለተበደሉ ነገር ግን በደላቸው ለእግዚአብሔር ላሳሰቡ በደለኞችንም በታላቅ ትዕግሥት ለታገሡና ከዚያም አልፈው በይቅርታ ልብ ለሚመለከቱ የሚያዘጋጀው ጸጋና ክብር አለው፡፡ በራሳቸው ለመበቀል ከሚጥሩ ግን ይህ ስጦታ የራቀ ነው፡፡ ወንድሞቹ በጭካኔ ለግብጻውያን የሸጡት ዮሴፍ በግብጽ ሀገር ግን ለታላቅ ሕዝብ ባለአደራ እስኪሆን ድረስ በባዕድ ሀገር ከፍ ከፍ እንዲል በማድረግ ስለተቀበለው መከራ የሰጠውን ክብር እናስብ፡፡ ወንድሞቹን በይቅርታ የሚያይ መልካም፣ ገር፣ ትሑትና የዋህ ልብ እንዳለው በኋላም በታሪኩ ተገልጦ እናያለንና፡፡ ስለዚህ ውድ ጠያቂያችንን ይህንንም በማሰብ ከበቀል መንፈስ መሸሽ ይገባዎታል፡፡

የክርስቲያን ወገን ግን ለሚደርስበት በደል፣ በቀልና ብድራቱ ከእግዚአብሔር ነው ብሎ በትዕግስት ለመጠባበቅ እምነት ያስፈልገዋል፡፡ እግዚአብሔር የበደለኞችን ግፍ ያያል፤ በደለኞችንም ይበቀላል፤ ይቀጣል፤ ተበድለው ለታገሱም ይክሳል፤ ጸጋና ክብሩን ያድላል ብሎ ለማሰብ በዚህ ሐሳብ ለመጽናትም ክርስቲያን መሆን ያስፈልጋል፡፡ ጠያቂያችንም በበቀል ተነሣሥተው ወደ ሌላ ፈተና የሚገቡ ከሆነ እምነትዎ፣ ፍቅርዎ፣ ትዕግስትዎ እየተፈተነ መሆኑን ማስተዋል ይገባዎታል፡፡ ስለዚህም ይህንን አስበው ከከንቱ የበቀል ስሜት መራቅ ይገባዎታል፡፡

ውድ ጠያቂያችን በእጅጉ የተቆጨት የእኅትዎ የሕይወት ዕቅድ ተሰናክሏል፤ ለስሜት ስብራት ተዳርጋለች ብለው በማሰብ ነው፡፡ ያንን መነሻ አድርገው የሚፈጽሙት የበቀል እርምጃ ደግሞ ኃጢአት ሆኖ እግዚአብሔርን ከማሳዘን አልፎ በወንጀልነቱ የሕግ መዘዝ ስላለው በቅጣት ሕይወትዎን ማባከንና ለከንቱ መንገላታት መዳረግ የሕይወትዎ አካሄድ ሁሉ ይጨነግፋል፡፡ አንዱን ቁስል ለመፈወስ ሌላ ቁስል መፍጠር ለእኅትዎም ሆነ ለእርስዎ ለመልካም የሚሆን አይደለም፡፡

ለዚህም ያዕቆብ ለልጆቹ ለስምዖንና ለሌዊ ያለውን ቃል ልናስተውስዎ እንወዳለን፡፡ የያዕቆብ ልጆች እኅታቸው ዲና በሴኬም እንደረከሰች ባወቁና እኅታቸው ባልተገረዘው ሰው በሴኬም እንደተደፈረች በተረዱ ጊዜ በራሳቸው እንደደረሰ የቤተሰቡን፣ የእምነታቸውን፣ የባህላቸውን፣ የወጋቸውን ክብር ሁሉ የነፈገ መሆኑን ባወቁ ጊዜ ሴኬምና ቤተሰቡን በመግደል፣ ከተማቸውንም በማውደም ተበቀሉ፡፡ ይህን ለማድረግ የሚያበቃ አስቆጪ ነገር ሴኬም ቢሠራም በወሰዱት የበቀል እርምጃ ግን ያዕቆብ የሚመጣበትን እንግልት አርቆ በማሰብ ‹‹በዚች አገር በሚኖሩ በከነዓናውያንና በፌርዛውያን ሰዎች የተጠላሁ ታደርጉኝ ዘንድ እኔን አስጨነቃችሁኝ፤ እኔ በቍጥር ጥቂት ነኝ፤ እነርሱ በእኔ ላይ ይሰበሰቡና ይመቱኛል፤ እኔም ከወገኔ ጋር እጠፋለሁ፡፡›› ብሎ ነበር፡፡ (ዘፍ ፴፬፥ ፴) ስለዚህ ለጊዜው እንደ ስምዖንና ሌዊ በበቀል ጊዜያዊ ደስታና ዕረፍት ቢገኝም በምድር ላይ ባለ የሰዎች የመበቃቀል፣ የመፈራረድ አካሔድ እንግልትና ስቃዩን በየቤተሰቡ ላይ መጨመሩን ማስተዋል ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ውድ ጠያቂያችን ያነሡት ጥያቄ በብዙ የተለያየ ዐውድ ውስጥ ይሁን እንጂ የብዙዎች ጥያቄ እንደሚሆን እናስባለን፡፡ ተበዳይ በቀልን ማሰቡ የሚዘወተር ቢሆንም ነገር ግን ለክርስቲያናዊ በቀል የማይገባ መሆኑን እንዲሁም ተበቃይም አግዚአብሔር መሆኑን በቃሉ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ በእምነት መንፈስ በመመላለስ የሚያምኑት አምላክ የተበዳዮችን መከራ የሚያይ፣ የሐዘናቸውንም ደረጃ የሚረዳ፣ የበዳዮችንም ማንነትና ጭካኔ ጥግ የሚያውቅ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የሚከፍል መሆኑን በማመን መረጋጋት አለብዎ እንላለን፡፡